# ትንቢተ አሞጽ (53)

## ጥናት አንድ አሞጽ 1፡1-15

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር አምላክ ዘመኑን ሁሉ እረኛ የነበረውና ስለ ትንቢት አገልግሎት ምንም ዓይነት እውቀት ያልነበረውን ሰው ከተጠቀመ፤ በእኛ ሕይወት ውስጥም ሊሰራ ያቀደው ነገር ኖሮ ተልዕኮን ሊሰጠን ከፈለግ፤ ሥራውን በእኛ ውስጥ የሚያከናውነው እርሱ ራሱ ስለሆነ፤ የእኛን ብቃትና ችሎታ ሳይሆን የልባችንን ፈቃደኛነት ብቻ እንደሚፈልግ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "በተቁሔ ከነበሩት እረኞች መካከል አንዱ የሆነው አሞጽ፣ ዖዝያን የይሁዳ ንጉስ በነበረ ጊዜ፤ እንዲሁም የዮአስ ልጅ ኢዮርብአም የእስራኤል ንጉስ በነበረ ጊዜ… ስለ እስራኤል ያየውና የተናገረው ቃል ይህ ነው።" አሞጽ 1፡1

1. አሞጽ 1፡1-15 በአንድነት ይነበብ። ቁ1 ላይ የሰፈረውን ሃሳብ ብቻ በመመልከት፤ አሞጽ ትንቢቱን የተናገረበትን ትክክለኛውን ጊዜ ለመጠቆም የተነገሩት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። አብዛኛዎቹ የእግዚአብሄርን የመልዕክት ለሕዝቡ ያስተላለፉትን ሰዎች ስንመለከት በዚህ ሥራ ልምድ የነበራቸውና ነብያት በመባል የታወቁ ሰዎች እንደነበሩ እናውቃለን፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንመለከተውና ለእስራኤል የእግዚአብሄርን መልዕክት ሲያስተላልፍ የምናየው ሰው የእለት ከእለት ተግባሩ ወይም ሥራው ምን ነበረ?
2. ቁ3፣ ቁ6፣ ቁ9፣ ቁ11ድንና፣ ቁ13ትን ስንመለከት እግዚአብሄር በእስራኤል ጎረቤት ሃገሮች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ እናነባለን። እግዚአብሄር በህዝቡ በእስራኤልም ላይ ሆነ በእነዚህ የአህዛብ መንግሥታት ላይ የሚፈርድበት ምክንያት አንድ ዓይነት ነው፤ ለነዚህ ሁሉ የፍርድ ምክንያት የሆነው ነገር ምንድነው? እነዚህን የእስራኤል ጎረቤቶች ሁሉ ስንመለከት ሁሉም አንድ የጋራ በሆነ ሥም ሃጥያት እንደሰሩ ይነገር እንጂ እግዚአብሄር እያንዳንዳቸውን የሚከስበት ነገር አንድ አይነት ሆኖ ታየዋለህ ወይ?
3. በእስራኤል ላይ ብቻ ሳይሆን የእስራኤልንም ጎረቤቶች ጨምሮ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሃጥያትን የመቅጣትና በሃጥያት ላይ ፍርድን የመስጠት መብት እንዳለው ሆኖ የምናገኘው ማንን ነው? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሲጠሩ የምናያቸው የእስራኤል ጎረቤት አገሮች ሁሉ ሃጥያትን መስራት ብቻ ሳይሆን፤ እግዚአብሄር ደግሞ በፍርዱ የሐጥያታቸውን ዋጋ እንደሚከፍላቸው እንመለከታለን፤ የእያንዳንዱ ፍርድ ላይ ስንመለከት ለሁሉም አንድ ተመሳሳይ የሆነ የፍርድ ቃል ሲናገራቸው እናያለን፤ ይህ ለሁሉም የተባለላቸው የፍርድ ንግግር ምን ነበረ?
4. ቁ9 ላይ ስናነብ "ስለ ሶስቱ የጢሮስ ሃጥያት፤ ይልቁንም ስለ አራቱ ቁጣዬን አልመልስም።" የሚለው አነጋገር ለጢሮስ ብቻ ሳይሆን ለደማስቆ፣ ለጋዛ፣ ለኤዶምና ለአሞንም ሁሉ ልክ ይህንኑ ቃል በቃል ነው የተጠቀመው። ሶስት ሃጥያትና አራት ሃጥያት ሲል፤ ሃጥያት የሰሩት ሶስት ወይም አራት ጊዜ ነው ማለት ነው ወይስ ምን ማለቱ ይመስልሃል? አገሮቹ ሁሉ በተለያየ ሐጥያት ሲከሰሱ፤ በዚህ ቁጥር ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ጢሮስን የሚከስበት ትልቁ ነገር ምንድነው? ከሰዎች ጋራ የምታደርገውን ቃል ኪዳን ማፍረስ በእግዚአብሄር ፊት እንደ ቀላል የማይወሰድ ነገር እንዳልሆነ ምን ያህል ተረድተሃል?
5. በቁ11-12 ላይ ኤዶምን በመወከል የሚታወቀው ሰው ማንነት ከዘፍ 36፡1 ላይ በማንበብ፤ ኤዶም ማን እንደሆነ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ማለትም አሞ 1፡11-12 ውስጥ ኤዶምን እግዚአብሄር ሊቀጣ ስለተነሳበት ሃጥያት ሲናገር "ርህራሄን በመንፈግ ወንድሙን በሰይፍ አሳዶታልና" ይላል። በዚህ ክፍል ውስጥ ስናነብ፤ እግዚአብሄር ከያዕቆብ (ከእስራኤል) ወንድም ከኤዶም ይጠብቅ የነበረው ነገር ምን ነበረ? ይህ ኤዶም ለወንድሙ ለእስራኤል ባለማድረጉ እግዚአብሄር የተቆጣበትን ሃጥያት ስንመለከት፤ ለራሳችን ህይወት ልንማረው የምንችለው እውነት ምንድነው?
6. በቁ13-15 ላይ ደግሞ አሞን የሚባለው በእግዚአብሄር ፊት ያደረገውን ክፉ ነገርና እግዚአብሄር ስለ ሃጥያቱ ሊከፍለው ያለውን በመዘርዘር ያሳየናል። ዘፍ 19፡36-38 ላይ ስታነብ የአሞን አመጣጥና የማን ዘር እንደሆነ ተናገር። በቁ13-15 ላይ አሞን የዚህ ዓይነት ጭካኔን እንዲያደርግ ምክንያት የሆነው ነገር ምን ነበረ?
7. ወደ ኋላ መለስ ብለን ቁ1ድን ስንመለከት፤ እግዚአብሄር ለእስራኤል መልዕክትን ለማስተላለፍ እስኪጠራውና አዲስ ተልዕኮን እስኪሰጠው ድረስ አሞጽ የሚያውቀው፣ ማድረግ የሚችለው፣ ወይም ደግሞ ተሰማርቶ የነበረበት የሥራ ዓይነት ምን ነበረ? አሞጽ ይህ ይህንን መልዕክት ለእስራኤል ይዞ እንዲሄድ ሲጠየቅ፤ ወደ ተላከበት አገልግሎት ላለመሄድ በአንተ አመለካከት ሊሰጣቸው ይችል የነበሩ ብለህ የምታስባቸውን ምክንያቶች ዘርዝር። አንተስ እግዚአብሄር እንድታደርግ ያዘዘህና ምክንያት ሰጥተህ ያለፍከው ነገር አለ ወይ? እግዚአብሄር እንድናደርገው የሚፈልገውን ነገር እንድናደርግ ሲጠይቀን የእኛን ችሎታ አይቶ ሳይሆን፣ እርሱ ከእኛ የሚፈልገው ታዛዥነታችንን ብቻ እንደሆነ ልናውቅ ያስፈልገናል።

# <u>ጥናት ሁለት አሞጽ 2፡1-16</u>

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር የእስራኤልን ጠላት ከቅርንጫፍ አልፎ ሥሩን እንደነቀለለት ሁሉ፤ ዛሬም በእኛ ህይወት ውስጥ ገዝፎና ራሱን ትልቅ አድርጎ ያስጨነቀንን ሁኔታ አምላካችን ስላልተለወጠ ከስሩ በመፈንቀል መታሰቢያ እንዳይኖረው ሊያደርግልን እንደሚችል ለመማር።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ቁመቱ እንደ ዝግባ፣ ጥንካሬውም እንደ ባሉጥ ዛፍ የነበረ ቢሆንም፤ አሞራዊውን ከፊታቸው አጠፋሁት፣ ከላይ ፍሬውን፤ ከታችም ሥሩን አጠፋሁ።" አሞ 2፡9

1. አሞጽ 2፡1-16 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-3 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር አምላክ በሁለት የአህዛብ መንግሥታት መካከል በተደረገው ነገር ውስጥ ገብቶ ፍርድ ሊሰጥ እንዳለ እንመለከታለን። በአሞ 1፡11 ላይ ኤዶም ላደረገው ክፋት ማለትም፤ ለወንድሙ ርህራሄን በመንፈግ በሰይፍ በማሳደዱ ምክንያት እንደሚፈርድበት እንደተናገር ስናይ፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ በኤዶም ላይ የተደረገበትን ክፋት በማየት ለኤዶም በመቆም ሞዓብን ለመቅጣት እንደተነሳ ስናይ፤ የእግዚአብሔርን ፍርድ አስመልክቶ ከእነዚህ ሁኔታዎች መማር የምንችለው ነገር ምን እንደሆነ ተናገር።
2. በቁ4 ላይ ነብዩ አሞጽ የአህዛብን ሃጥያት መናገር አቁሞ የይሁዳን ሃጥያት ሲዘረዝር እንመለከታለን። ይህንን ቁጥር ስንመለከት "ስለ ሶስቱ የይሁዳ ሃጥያት፣ ይልቁን ስለ አራቱ ቁጣዬን አልመልስም" ይላል፤ ከዚህ አነጋገር ስናይ በይሁዳና በአህዛብ መሃል ሃጥያትን አስመልክቶ ምን ልዩነት እናያለን? ከዚሁ ከቁ4 ውስጥ ሳንወጣ፤ ይሁዳ በእግዚአብሄር ላይ ያደረጋቸው ሃጥያቶች አድርጎ የሚዘረዝራቸው ሶስት ነገሮች እናነባለን፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ለእያንዳንዱ መንግሥት ሃጥያቱን የሚቀጣው ምሽጎቻቸውን በማቃጠል እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ውስጥ ቁ4፣ 7፣ 10፣ 12፣ 14 የተመለከትን ሲሆን፤ ይሁዳም በአሞ 2፡5 ላይ በሃጥያቷ ምክንያት የሚቃጠለው የይሁዳ ምሽግ ኢየሩሳሌም እንደሆነ ይናገራል፤ የዚህች ከተማ በእሳት መቃጠል እንደ ትልቅ ነገር ሆኖ የሚታየው ለምንድነው? ትንቢቱ በተነገረበትና በኤር 52፡13 ላይ ናቡከደነጾር ከተማይቱን ባቃጠለበት መሃል ቢያንስ የ200 ዓመታት ልዩነት እንዳለ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይናገራሉ፤ ታዲያ ይህንን ስንመለከት የእግዚአብሄርን ፍርድ አስመልክቶ ልንማር የምንችለው እውነት ምንድነው?
4. በቁ6-7 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በእስራኤል ሐጥያት ላይ ከመፍረድ እንደማይመለስ ይናገራል። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የእስራኤልን ድርጊቶች ሲዘረዝር የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን የሚዘረዝር ሲሆን ተበዳዮች ሆነው የተዘረዘሩትን ቢያንስ አራት ዓይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር። እስራኤል እነዚህን ነገሮች ሁሉ  ምስኪንና ምንም ማድረግ ሃይል ወይም ችሎታ በሌላቸው ሰዎች ላይ የሚያደርጓቸውን ድርጊቶች በሁሉ፤ እግዚአብሄር በማን ላይ እንደሚያደርጉት አድርጎ ነው በቁ7 ላይ የሚናገረው?
5. እነዚህ ሰዎች የፈለጉትን ዓይነት ኑሮና እግዚአብሄር የሚጸየፈውን ዓይነት ሕይወት ይኑሩ እንጂ አምልኮና መስዋዕት ማድረጋቸውን እንዳላቋረጡ ከቁ8 መረዳት እንችላለን። በመሰዊያው አጠገብ ወይም በአምላካቸው ቤት የሚጠቀሙባቸውን ዕቃዎች ስትመለከት መገኛቸው ከየት ነው? እነዚህ ሰዎች በግፍና በሃጥያት የተገኘውን ቁሳቁስ በአምላካቸው ቤተ መቅደስ አምጥተው እነደተጠቀሙ፤ ዛሬስ በዚህ ዘመን በእግዚአብሄር ቤት ውስጥ የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ይኖር ወይም አይኖር እንደሆነና በሁኔታው ላይ ውይይት ይደረግበት።
6. በቁ9-11 ላይ እግዚአብሄር ለሕዝቡ ለእስራኤል ቀድሞ ያደረገላቸውን ነገሮች ይዘረዝርላቸዋል። በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሄር ጠላቶቻቸው የነበሩትን አሞራውያንን እንደምን አድርጎ ነው የሚስላቸው? እግዚአብሄር አምላካቸው የእስራኤልን ጠላት በማጥፋት ብቻ ተወስኖ የቀረ እንዳይደለና ሌላም ለህዝቡ ያደረገላቸው ነገሮች እንደነበሩ በዚህ ክፍል ውስጥ ይናገራል፤ እነዚህ እግዚአብሄር ለእስራኤል ያደረጋቸው ተጨማሪ ነገሮች ምን ምንድናቸው?
7. ቁ12-16 ላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ጠላቶቻቸውን አጥፍቶ በጽድቅ እርሱን እያከበሩ ሊኖር የሚያስችሏቸውን ስጦታዎች እንደሰጣቸው በቁ11 ላይ ያየናቸውን ሰዎች በምን ዓይነት መንገድ ነው ሕዝቡ ያስተናገዷቸው?
8. በቁ9 ላይ ስናነብ በእስራኤል ፊት አስፈሪና የማይበገር ሆኖ የሚታየውን ጠላቱን እግዚአብሄር በማያዳግም መንገድ ዓይነት መንገድ እንደመታው ይናገራል፤ በዚህ ቁጥር ላይ የጠላታቸው ሽንፈት ከባድ መሆኑን የምናየው እንዴት ነው? ያስፈራራህን ጠላት እግዚአብሄር እንዳያንሰራራ አድርጎ የመታልህ የምታስታውሰው ጊዜ ካለ ለወገኖች አካፍል። እግዚአብሄር የሚያስፈራራንን ጠላታችንን ሲመታ በቅርንጫፍና በፍሬው ላይ ብቻ በማተኮር ሳይሆን ከሥሩ በመንቀል ቅሬታ እንዳይኖረው በማድረግ የማያዳግም ድል እንደሚሰጠን ከዚህ ክፍል እንረዳለን።

# ጥናት ሶስት አሞጽ 3:1-15

የጥናት ዓላማ፡- እስራኤል በእግዚአብሄር መወደዷና የበለጠ ወደ እርሱ መቅረቧ ከቅጣት ነጻ የሚያደርጋት ነገር ሳይሆን እንዲያውም የበለጠ ተጠያቂ እንዳደረጋት ሁሉ፤ በዘመናችንም ሰው ፓስተር፣ ሐዋርያ፣ ነብይ ወይም ማንኛውንም ዓይነት ጥሪ ተቀብያለሁ ቢል፤ ከስጦታው ጋራ አብሮ የሚመጣ ተጠያቂነት እንዳለና ቅጣቱም ሊከተል እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “ከምድር ወገን ሁሉ እናንተን ብቻ መረጥሁ፤ ስለዚህ ስለሰራችሁት ሃጥያት ሁሉ እኔ እቀጣችኋለሁ።” አሞ 3:2

1. አሞጽ 3:1-15 በአንድነት ይነበብ። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እግዚአብሄር ብዙ ጊዜ እየደጋገመ የሕዝቡ መነሻው ከየት እንደነበረ ሲያስታውሳቸው ይታያል፤ በቁ1-3 ውስጥ ስንመለከት እግዚአብሄር ይህንን መነሻቸውን እንዲያዩ የተናገረውን ሃሳብ የምናየው የትኛው ሃሳብ ላይ ነው? እነዚህኑ ቁጥሮች በምታነብበት ጊዜ፤ እስራኤል ወደ ሃጥያትና እግዚአብሄርን ወደ ማሳዘን ከመሄድ ይልቅ ለምሥጋናና ለአምልኮ ሊያነሳሳት የሚችል የተደረገላት ምን ነገር ትመለከታለህ?
2. ቁ3 ላይ ስንመለከት ነብዩ አሞጽ ስለሁለት ሰዎች አብሮ መጓዝ ማለትም፤ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ አብረው መጓዝ እንደማይችሉ አድርጎ ይናገራል፤ ነብዩ የሚናገርላቸው እነዚህ ሁለት ተጓዦች የሚላቸው እነማን እንደሆኑ ነው የምትረዳው? “በውኑ ሁለት ሰዎች ሳይስማሙ አብረው መጓዝ ይችላሉን?” የሚለው ሃሳብ በዚህ ክፍል ዓውድ መሰረት ስትመለከተው አብረው መሆን ስለማይችሉ ይለያዩ ማለቱ ነው ወይስ ሌላ ሃሳብ ሊኖረው ይችላል ብለህ ታምናለህ? እግዚአብሄር ልክ አይደለህም እያለን እኛ ደግሞ ነገራችንን ለማስተካከል ፈቃደኛ ሳንሆን ሕብረታችን እንደድሮው ሊቀጥል እንደማይችል ልንረዳ ያስፈልገናል።
3. በቁ4-6 ውስጥ እግዚአብሄር አምላክ በእስራኤል ላይ ሊወስድ ያለውን እርምጃ እንዲረዱት ለማድረግ ሶስት ዓይነት ምሳሌዎችን በማንሳት ሲናገር እናገኘዋለን። እነዚህ በዚህ ሥፍራ የተነገሩት ሶስቱ ምሳሌዎች ምን ምን እንደሆኑ አጠር ባለ መንገድ ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተመለከትናቸው ሶስቱ ምሳሌዎች እግዚአብሄር ከሕዝቡ ጋራ በአሁኑ ወቅት ካለው ግንኙነትና ሊወስድ ካለው እርምጃ ጋራ ሊኖራቸው የሚችለው ግንኙነት ምንድነው ትላለህ?
4. በቁ4-6 የተመለከትናቸው ሶስቱ ምሳሌዎች ሊመጣ ላለው ነገር እርግጠኛነት የተነገሩ ከሆነ፤ ምሳሌዎቹ ለእስራኤል ሰዎች በዚህ ሰዓት መነገራቸው ዋነኛ ምክንያት ሊሆን ይችላል የምትለው ነገር ምንድነው? በቁ7 ላይ “በእውነት ጌታ እግዚአብሄር ምሥጢሩን ለአገልጋዮቹ ለነብያት ሳይገልጥ ምንም ነገር አያደርግም።” ይላል። በዚህ ዓውደ ምንባብ ውስጥ ከምንመለከተው፤ እግዚአብሄር እንደ ምሥጢር አድርጎ የሚናገረው ነገር ምኑን ነው ብለህ ታምናለህ?
5. በቁ8-10 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ እንደ ምስክር አድርጎ አስቀድመው እስራኤልን በመጨቆን የሚታወቁትን ግብጽንና አዛጦንን (ፍልስጤምን) ሲጠራ እንመለከታለን። ለምን ይመስልሃል እግዚአብሄር በዚህ ሥፍራ ራሳቸው ክፉና ጨካኝ የሆኑትን የአህዛብ መንግሥታት የሕዝቡን ገመና እንዲያዩ የሚጠራው? በቁ10 ላይ “በጎ ነገር ማድረግን አያውቁም” ሲል በጎ ነገር ምን እንደሆነ እውቀቱ የላቸውም ለማለት ነው ወይስ እግዚአብሄር ይህንን ሲናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ሥነ ምግባራችን ከአሕዛብ እንኳን አንሶ ሲገኝ ምን ያህል እግዚአብሄር ያዝን ይሆን?
6. እግዚአብሄር አምላክ ሕዝቡ እስራኤል የሚኖረውን የህይወት ዓይነት ከዘረዘረ በኋላ፤ በቁ11-15 ላይ ደግሞ በሃጥያታቸው ምክንያት ሊያመጣባቸው ያለውን ፍርድ ይነግረናል። በቁ11 ላይ እግዚአብሄር በነብዩ አሞጽ አማካኝነት ጠላቶቻቸው መጥተው እንደሚያደርጉ የተናገራቸው ሶስት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በቁ14 መሰረት እግዚአብሄር እስራኤልን በሚቀጣበት ቀን የሚያፈርሳቸው ሁለት ዓይነት የተለያዩ ነገሮች እንዳሉ ያሳየናል፤ እነዚህ ሁለት ዓይነት ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
7. እስራኤል ለእግዚአብሄር ቅርብ የሆነችና በእርሱ የተመረጠች ሆና ሳለ፤ ስለ ሐጥያቷ ግን እንደሚቀጣት በቁ2 ላይ ሲናገራት እንመለከታለን፤ እግዚአብሄር ከምድር ወገኖች ሁሉ የወደዳትን እስራኤልን ስታጠፋና በሐጥያት ስትገኝ መቅጣቱ ለእኛ ምን ያስተምረናል ትላለህ? የምትወደውን ልጅህ ሲያጠፉ ቀጥተህ፣ ወይም ደግሞ አጥፍተህ ስትገኝ በምትወዳቸው ቤተሰቦችህ እጅ ተቀጥተህ ታውቃለህ ወይ? እያንዳንዱ የጌታ ልጅ፤ በእግዚአብሄር ቤተሰብ ውስጥ ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ እንደሚጠበቅበትና፤ ከብዙ ስጦታ ጋራ ብዙ ሃላፊነትም አብሮት ስለሚመጣ የስጦታውን ብዛት ማቃለል ለበለጠ ፍርድ እንደሚያስከትል መገንዘብ ተገቢ ነው።

# ጥናት አራት አሞጽ 4፡1-13

የጥናት ዓላማ፡- እስራኤልን ወደ ትክክለኛ ሕይወት ለመመለስ በከባድ ሁኔታዎች ውስጥ እንዳሳለፋቸው ሁሉ፤ እኛም ምንም እንኳን ለጊዜው ደስ ባያሰኘንም፤ እግዚአብሄር በልጆቹ ሕይወት ውስጥ የሚፈቅዳቸው ሁኔታዎች ሁሉ ለእድገታቸው ወይም ደግሞ በበለጠ ወደ እርሱ ለማስጠጋት እንጂ ጉዳታቸውን ፈልጎ አንዳችም ነገር እንደማያመጣ ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- “በየከተማው ሆዳችሁን ባዶ አደረግሁት፤ በየመንደሩም የምትበሉትን አሳጣኋችሁ፤ እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም ይላል እግዚአብሄር” አሞ 4፡6

1. አሞጽ 4፡1-13 በአንድነት ይነበብ። በቁ1 ላይ እግዚአብሄር አምላክ ነብዩ በኩል የሚያስተላልፈውን መልዕክት እንዲሰሙለት የሚናገራቸው ፍጥረታቱ እነማን ናቸው? መጽሐፍ ቅዱሳችንን በአጠቃላይ ስንመለከት እግዚአብሄር ስለ ድሆችና፣ ስለ ችግረኞች ያለውን አመለካከት ግልጽ አድርጎ በማያጠያይቅ መንገድ ተናግሯል፤ ይህን ክፍልና ሌሎችንም ትዝ የሚሉህን ጥቅሶች በማሰብ፤ እግዚአብሄር ስለድሆችና ስለችግረኞች የሚሰማው ስሜት ምን እንደሚመስል የተረዳኸውን ተናገር።
2. በቁ2-3 ከምናነበው አነጋገር እነዚህ እግዚአብሄር ወደ ፍርድ እንደሚሄዱ የሚናገርላቸው ሰዎች በግዴታ እንጂ ወደው እንደማይሄዱ የሚጠቁመን ሃሳብ የትኛው ነው? በቁ2 ላይ ስናነብ እግዚአብሄር “ትሩፋናችሁ እንኳ በአሳ መንጠቆ የሚወሰድበት ጊዜ ይመጣል” ይላል። ይህንን ያህል እግዚአብሄር በእነርሱ ላይ ለመፍረድ ካሰበና ውሳኔ ካደረገ፤ ውሳኔውን በሥራ ላይ ለማዋል ማናቸውንም ነገር ማድረግ የሚችል ሆኖ ሳለ፤ ለምን ይመስልሃል ወዲያውኑ በዚያኑ ሰዓት የማያደርገው?
3. በቁ4 እና 5 ላይ ስንመለከት እነዚህ ሰዎች እንደ እስራኤላዊና ሕጉን እንደሚያውቅ ሰው እየተለማመዱቸው ያሉትን ነገሮች ይጠቁመናል፤ እየተለማመዱቸው ያሉትና እግዚአብሄር በማሾፍ መልክ እንዲቀጥሉበት የሚነግራቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ተናገር። እነዚህ ሰዎች በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ እየተለማመዱ የሚታዩት ሃይማኖታዊ ድርጊቶችና፤ በቁ1 ላይ ደግሞ ስለነዚሁ ሰዎች የተነገረውን ነገር በምታነብበት ጊዜ ድርጊታቸውን ግብዛዊ ነው ማለት የሚያስችለን ነገር ምንድነው? አንተስ እሁድ በምታሳልፈው የአምልኮ ጊዜና ከሰኞ እስከ ቅዳሜ የምትኖረው የሕይወት ዓይነት ሲታይ ግብዝ ሊያሰኝህ የሚችል ነገር ይኖር ይሆን?
4. እስራኤላውያኑ እያደረጓቸውና እያካሄዷቸው ላሉት ሐይማኖታዊ ድርጊቶች እግዚአብሄር የሚሰጠው ግምትና እነርሱ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት የተለያየ እንደሆነ እንመለከታለን፤ እነርሱ ለድርጊታቸው የሚሰጡት ግምት ቁ5ትን ስንመለከት ምን ይመስላል?
5. ከቁ6 አንስቶ እስከ ቁ11 ድረስ ባሉት ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሄር አምላክ በድርጊቶቻቸው ደስተኛ አለመሆኑን ለመግለጽ በእነርሱ ላይ ያመጣቸውን የተለያዩ ነገሮች ሰፍሮ እናገኛለን። በተለይም በቁ7 ላይ የተነገረው የእግዚአብሄር አደራረግ በምን መንገድ ነው እስራኤላውያን እውነትም ይህ ድርጊት ከእግዚአብሄር መሆን አለበት ሊያሰኛቸው የሚችለው ሁኔታ ምኑ ነው ትላለህ?
6. በቁ12 ላይ “አምላክህን ለመገናኘት ተዘጋጅ” የሚል አረፍተ ነገርን እናነባለን፤ በዚህ ክፍልና በዚህ ዓውደ ምንባብ ውስጥ ስትመለከት ይህ እግዚአብሄርን መገናኘት የሚለው ሃሳብ ብዙ ጊዜ በአማኞች ዘንድ እንደሚጠቀሰው ለመልካም የተነገረ ነው ወይስ ሌላ ሃሳብ ታያለህ? በዚህ ክፍል ውስጥ እስራኤላውያን ለመገናኘት ተዘጋጁ በመባል የተነገራቸው አምላክ በጥቂቱ ማንነቱን በዚያው በቁጥር 13 ላይ ያስተዋውቃል፤ እግዚአብሄር ራሱን የሚያስተዋውቅባቸውን ሃሳቦች በመዘርዘር ተናገር።
7. እግዚአብሄር አምላክ ብዙና የተለያዩ እስራኤላውያንን የሚያስጨንቁ ነገሮችን በእነርሱና በአገሪቱ ላይ አድርጎ ሳለ “እናንተ ግን ወደ እኔ አልተመለሳችሁም” በማለት በተደጋጋሚ ሲናገራቸው እናነባለን፤ ምንም እንኳን እስራኤልን በጊዜው ደስ የማያሰኝ እንኳን ቢሆን እግዚአብሄር ያደረገውን ያደረገበት ምክንያት ለምን እንደነበረ ነው የምናየው? በሕይወትህ የሚያልፉ አንዳንድ ነገሮችን ለበጎ ሊሆኑልህ እንደሚችሉ አስበት ታውቃለህ ወይ? ምንም እንኳን ለጊዜው ደስ ባያሰኘንም እንኳን፤ እግዚአብሄር በልጆቹ ሕይወት ውስጥ የሚፈቅዳቸው ሁኔታዎች ሁሉ ሊያሳድጉን ወይም ደግሞ በበለጠ ወደ እርሱ ሊያስጠጉን እንጂ ለጉዳታችን እንደማይመጡ መረዳት ይኖርብናል።

# ጥናት አምስት አሞጽ 5፡1-27

የጥናት ዓላማ፡- በእግዚአብሄር ቃል ሊገስጹን በፍቅር ወደ እኛ የሚመጡትን ሰዎች በጥላቻ ብናስተናግድ፥ እውነትንም ደግሞ በግልጽነት የሚናገሩንን ወገኖች በንቀት ብንመለከታቸው እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ እንደተናገረው ሁሉ የበረከት እጁን ከእኛ ሊያነሳ እንደሚችል፤ ስለዚህም ደግሞ ልፋትና ጥረታችን ሁሉ ፍሬ አልባ ሊሆንብን እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "እናንተ በፍርድ አደባባይ የሚገሥጻችሁን ትጠላላችሁ፤ እውነት የሚናገረውንም ትንቃላችሁ… ስለዚህ በተጠረበ ድንጋይ ቤት ብትሰሩም በውስጡ ግን አትኖሩም፤ ባማሩ የወይን ተክል ቦታዎች ወይን ብትተክሉም፤ የወይን ጠጁን ግን አትጠጡም" አሞ 5፡10-11

1. አሞጽ 5፡1-27 በአንድነት ይነበብ። በቁ2 ላይ ስናነብ እስራኤል እንደወደቀችና ተመልሳ እንደማትነሳ አድርጎ እግዚአብሄር ሲናገር እንሰማዋለን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በቁ4 ላይ እርሱን በመፈለግ በህይወት ሊኖሩ እንደሚችሉ ይነግራቸዋል። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች የሚናገሩት የተለያዩና የማይገናኙ ሃሳቦች ይመስላሉ፤ ታዲያ እግዚአብሄር እስራኤል ወድቃለች መነሳት አትችልም ሲል ምን ለማለት ፈልጎ ነው ትላለህ? በቁ3 ላይ እስራኤል ብርቱ የሆኑ ሰራዊቶቿን እንኳን ለጦርነት ብታስከትት ውጤቱ አርኪ እንደማይሆን እግዚአብሄር ይነግራቸዋል፤ የጦርነቱ ውጤትና የሂሳቡ ስሌት ምን እንደሚመስል ቁ3 የሚናገረውን ሃሳብ አብራራው።
2. በቁ4 እና በቁ5 ውስጥ ስንመለከት ለእስራኤል ሕዝብ በሕይወት ለመኖር ከፈለገ ማድረግ ያለበት ምን እንደሆነ ሲነገራቸው እናንባለን፤ በሕይወት ለመኖር ከፈለጉ ማድረግ የሚኖርባቸው ነገር ምንድነው? "በሕይወት መኖር" የሚለው አነጋገር እስትንፋስ እንዲኖራችሁ ወይም ደግሞ እንዳትሞቱና ቀናቶቻችሁ እንዲራዘሙ ብቻ ለማለት ነው ወይስ ከዚያ ያለፈ ሃሳብ ያዘለ ይመስልሃል? በሕይወት ለመኖር እነዚህ ሰዎች ያደርጓቸው የነበሩና ያንን ማድረግ እንደማይጠቅማቸው የተናገራቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? አንተስ ያረፈና ሰላም የሞላበትን የደስታ ሕይወት ለመኖር የምታሳድደው የተለየ ነገር አለህ ወይስ የዚያ ሁሉ ምንጩ እግዚአብሄር መሆኑን ተረድተሃል?
3. በቁ7-9 ላይ የነብዩ አሞጽ ትንቢት ያተኮረባቸውና ያነጣጠረባቸውን ሁለት ዓይነት ሰዎች እንመለከታለን፤ እነዚህ በዚህ ክፍል ውስጥ ትኩረት የተሰጣቸውና ትንቢቱ የሚነገርላቸው ሰዎች እነማን ናቸው? በቁ8 እና በቁ9 ላይ የተነገረው የእግዚአብሄር ባህርይና ማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ለመግለጽ መሞከሩ በቁ7 ላይ ከተጠቀሱት ሰዎች ድርጊትና ባህርይ ጋራ ሊገናኝ የሚችልበት ምን መንገድ አለው? ዛሬ ማንም ምንም ሊያደርገኝ አይችልም ብሎ የተዝናና ሁሉ ምሽግን ማፍረስ የሚችለው እግዚአብሄር ሊደርስበት እንደሚችል ሊረዳ ያስፈልጋል።
4. በቁ10 ውስጥ ስንመለከት በእስራኤላውያኑ ሕብረተሰብ መካከል ተቀባይነት የሌላቸውና የማይፈለጉ ሁለት ዓይነት ሰዎችን በማንሳት ይናገራል፤ እነዚህ በእስራኤላውያን ዘንድ ተቀባይነትን ያጡት ሁለት ዓይነት ሰዎች እነማን እንደሆኑ ተናገር።
5. በቁ11-12 ላይ እነዚህ እስራኤላውያን የሚፈጽሟቸው ሌሎችም ግፎችና ሃጥያቶች ተዘርዝረዋል፤ በነዚህ ቁጥሮች ላይ የተነገሩት ሃጥያቶቻቸው ምን ምን እንደነበሩ ተናገር። በቁ13-15 ውስጥ ደግሞ እግዚአብሄር ከእነርሱ ጋራ እንዲሆን ከፈለጉና ለዮሴፍ ቤት ቅሬታ እንዲራራ ከፈለጉ ማድረግ የሚኖርባቸውን የተለያዩ ሃሳቦች ነግሯቸዋል፤ እነዚህ የተናገራቸው ሃሳቦች ወይም ምክሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ምክሮች ለእኔና ለአንተስ ሕይወት ምን ያህል አስፈላጊ አድርገህ ትመለከታቸዋለህ?
6. አብዛኛውን ጊዜ በጸሎቶቻችን ውስጥ እግዚአብሄር አምላክ በመካከላችን እንዲያልፍ አጥብቀን እንለምነዋለን፤ በቁ16-20 ላይ ስናነብ በተለይም በቁ17 ላይ "እኔ በመካከላችሁ አልፋለሁና ይላል እግዚአብሄር።" በማለት የተናገረው አነጋገር እኛ በጉባኤአችን መሃል እንዲያልፍ ከምንለምነው ዓይነት ሃሳብ የሚለየው በምን መንገድ ነው?
7. በቁ21-27 ላይ እግዚአብሄር ምን ያህል በሕዝቡ አኗኗርና መንፈሳዊ ሕይወት ደስ እንዳልተሰኘ የሚገልጽባቸውን አነጋገሮች ከባድ በሆኑና ከእግዚአብሄር አንደበት የወጡ በማይመስሉ ሃሳቦች ሲገልጽ ይታያል። ሕዝቡ በቁ21-23 ለእግዚአብሄር ከማድረግ እንዲያቆሙ የተነገሯቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው? እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንዲያቆሙና እንዲያስወግዱ ከነገራቸው በኋላ፤ በእነዚህ ነገሮች ምትክ እንዲለማመዱ የሚነግራቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምንድናቸው? አንተስ ሃይማኖታዊ ነገር በማከናወን ተይዘሃል፥ ወይስ ፍርድንና ጽድቅን በማድረግ ትበረታለህ?
8. ወደ ቁ10 ላይ ተመልሰን ስንመለከት፤ የሚገስጻቸውን ሰው የሚጠሉትንና፣ እውነትን የሚነግራቸውን ሰው የሚንቁትን ሰዎች እግዚአብሄር አምላክ በቁ11 ላይ የዚህ ድርጊታቸው ውጤት ምን እንደሆነ ነው የሚነግራቸው? አንተስ ወንድሜ፣ አንቺስ እህቴ በእግዚአብሄር እውነት የሚገስጹህን ወገኖች በጥላቻ፤ እውነትን የሚነግሩህን ደግሞ በንቀት ታስተናግዳቸዋለህ ወይ? በእግዚአብሄር ቃል ሊገስጹን በእግዚአብሄር ወደ እኛ የሚላኩትን ሰዎች በጥላቻ ማስተናገድና፥ እውነትን የሚነግሩንን ወገኖች በንቀት አመለካከት ማየት የማይገባ ድርጊት እንደሆነ ልንረዳ ያስፈልገናል።

<u>ጥናት ስድስት አሞጽ 6፡1-7፡17</u>

የጥናት ዓላማ፡- አንድ ሰው በቤተ ክርስትያን ውስጥ ትልቅ ቦታ ይዞ ስለተቀመጠና ስም ብቻ ስላለው የእግዚአብሄርን ትክክለኛ ድምጽ መለየት ይችላል ማለት እንዳልሆነ፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ አሜሲያስ በነብዩ በአሞጽ ላይ እንደተነሳበት ሁሉ በእግዚአብሄር እውነተኛ አገልጋዮች ላይ በመነሳት ሌሎች ሊያደርሱ ከሚችሉት ጉዳት በላይ በአገልጋዮች ላይ ሊያደርስ እንደሚችል ለመማር።

የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "አሜሲያስም አሞጽን እንዲህ አለው፤ አንተ ባለ ራዕይ ከዚህ ሂድ! ከይሁዳ ምድር ሽሽ፣ እዚያም እንጀራህን ብላ፤ በዚያም ትንቢት ተናገር። ከእንግዲህ ወዲያ ግን በቤቴል ትንቢት አትናገር…።" አሞ 7፡12-13

1. አሞጽ 6፡1-7፡17 በአንድነት ይነበብ። በቁ1-2 ላይ ስናነብ በተለይም ቁ1 መልዕክቱን ለሚያስተላልፍላቸው ሰዎች መለያ አድርጎ የሚጠቀምባቸውን ሶስት ዓይነት ነገሮች እናነባለን፤ እነዚህ ሶስት መለያዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር። በእነዚህ ሶስት ነገሮች መለያቸው የሆኑትን ሰዎች ማንነታቸውንም በዚሁ ቁጥር ላይ ነብዩ ጠቅሶት እናገኘዋለን፤ እነዚህ ሰዎች እነማን ናቸው? በነዚህ ሁለት ቁጥሮች ውስጥ ደግሞ እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን እንዲያስተያዩ እግዚአብሄር የሚጋብዛቸው ከየትኞቹ ከተሞች ጋራ ነው?
2. ከቁ3-6 ባሉት ቁጥሮች ውስጥ እስራኤላውያን እንደሚያደርጓቸውና ትክክል እንዳልሆኑ አድርጎ ነብዩ የሚናገራቸውን የተለያዩ ነገሮች እንመለከታለን፤ ይህ ማለት ለምሳሌ ከዝሆን ጥርስ ባጌጠ አልጋ ላይ መተኛት፣ ወይም ከበግ መንጋ ውስጥ ጠቦት መብላት፣ ወይም ደግሞ ባልተቃኘ ሙዚቃ መሳሪያ መዘመርና የመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ በራሳቸው ሃጥያት ናቸው ማለቱ ነው ወይ? እነዚህ ነገሮች በራሳቸው ሃጥያት አይደሉም ካልን ደግሞ፤ ታዲያ በዚህ ዓውድ መሰረት ሃጥያት የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው ትላለህ?
3. ከቁ7 እና ቁ8 ከምንመለከተው ሃሳብ ተነስተን፤ እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ስለ እስራኤል በዚያን ወቅት በሕዝቡ ሕይወት ውስጥ የሚያያቸውና የተጸየፋቸው ምን ዓይነት ነገሮችን መጥቀስ እንችላለን? በቁ12 ላይ ፈረሶች በጭንጫ ላይ እንደማይሮጡ፤ ሰው ደግሞ ባህርን በበሬ እንደማያርስ ተናግሮ፤ ነገር ግን በማለት እነርሱ የሚያደርጓቸውን ነገሮች መናገሩ እነርሱን ምን ሊላቸው ፈልጎ ነው ትላለህ?
4. እግዚአብሄር አምላክ የሚያስጨንቀንን ሁሉ በእርሱ ላይ እንድንጥል በ1ኛ ጴጥ 5፡7 ላይ እየተናገረን፤ በዚህ ክፍል በቁ14 ላይ ስናነብ ደግሞ "የእስራኤል ሕዝብ ሆይ እኔ ከሃማት መግቢያ እስከ አረባ ሸለቆ ድረስ የሚያስጨንቃችሁን ሕዝብ በእናንተ ላይ አስነሳለሁ።" በማለት ይናገራል። እንዴት ነው እግዚአብሄር በአንድ በኩል ሕይወታችንን ከጭንቀት የምናሳርፍበት መሸሸጊያ አምባ የሚሆነን፤ በሌላ በኩል ደግሞ ለጭንቀታችን ምክንያት ሆኖ ሊገኝ የሚችለው እንዴትና ለምንድነው? ለአንተስ እግዚአብሄር የሰላምህ ምክንያት ነው ወይስ ለጭንቀትህ?
5. በአሞ 7፡1-6 ላይ እግዚአብሄር በእስራኤል ላይ ሊያደርግ ያለውን ክፉ ነገር ሄዶ እንዲናገር ለባርያው ለነብዩ አሞጽ ሲያስታውቀው እንመለከታለን። እግዚአብሄር ሊያደርጋቸው የነበሩት ሁለቱ የተለያዩ መቅሰፍቶች በእስራኤል ላይ እንዳይደርሱ የተከለከሉት በምን ምክንያት ነው? አሞጽ የእግዚአብሄርን መልዕክት ለሕዝቡ እንዲያስተላልፍ የተጠራ ነብይ ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ስንመለከተው ግን ከነብይነት ያለፈ አድራጎት ሲያደርግ ነው የምናየው፤ ይህ የአሞጽ ድርጊት ምን ሊያስተምረን ይችላል ትላለህ?
6. በቁ10-11 ላይ ስናነብ "አሞጽ በእስራኤል ቤት መካከል በአንተ ላይ እያሴረ ነው" በማለት የቤቴሉ ካህን የሆነው አሜስያስ ለንጉሱ ኢዮርብአም ሲነግረው እናያለን። ነብዩ አሞጽ ምን በማለት የተናገረው ትንቢት ነው በአሜስያስ ዘንድ ሴራ ሆኖ የተቆጠረበት?
7. ቁ14-17 ላይ ስንመለከት አሞጽ ስለራሱ ማንነት፣ አገልግሎቱና ተልዕኮ ለካህኑ ለአሜስያስ ሲያብራራለት እናያለን፤ እነዚህ ቁጥሮች ስለ እግዚአብሄር መልዕክተኛ የተነገሩትን ነገሮች ተናገር። በእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ይህ የእግዚአብሄር መልዕክት ለህዝቡ እንዳይተላለፍ የሞከረው ካህኑ አሜስያስ ካደረገው ነገር የተነሳ ለግሉ የተነገረለት ነገር ምንድነው?
8. የእግዚአብሄር መልዕክተኛ የሆነውን ነብዩን አሞጽን በ7፡12-13 ላይ ትንቢት እንዳይናገር እንደተከለከለ እናነባለን፤ ትንቢት እንዳይናገር ከመከልከሉ ባሻገር በተለይም እንዳይናገር የከለከለው ሰው ማንነት ሁኔታውን የበለጠ አስገራሚ የሚያደርገው ነገር በአንተ አመለካከት ምን ታያለህ? የእግዚአብሄርን ድምጽ ያንላል ወይም ያበረታታል ያልከው ሰው ድምጹን ለማዳፈን የሞከረ ሰው ገጥሞህ ያውቃል ወይ? አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሄር ነብያት የተቀበሉትን መልዕክት ወደ እግዚአብሄር ህዝብ እንዳይደርስ የምንከለክል መሪ ሆነን እንዳንገኝ ልንጠነቀቅ ያስፈልጋል።

# ጥናት ሰባት አሞጽ 8፡1-9፡15

የጥናት ዓላማ፡- ዛሬ የእግዚአብሄር ቃል በሰፊው ያለ አንዳች ገደብ መስማት፣ ማንበብ፣ መማርና ማጥናት የምንችልበት ሰፊ የሆነ በር እግዚአብሄር ለእኛ ለሁላችን ከፍቶልናል፤ ሆኖም ይህንን ሰፊ በር ካልተጠቀምንበት፤ ዛሬ በፊታችን ያለን ዓይነት ነጻነት ሁልጊዜ ይኖረናል ብሎ ማሰብ ሞኝነት እንደሆነ ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- "ጌታ እግዚአብሄር እንዲህ ይላል፤ በምድር ላይ ረሃብን የምሰድበት ዘመን ይመጣል፤ ይኸውም የእግዚአብሄርን ቃል የመስማት ረሃብ እንጂ እንጀራን የመራብ ወይም ውሃን የመጠማት አይደለም።" አሞ 8፡11

1. አሞጽ 8፡1-9፡15 በአንድነት ይነበብ። በዚህ ሥፍራ ማለትም በአሞ 8፡1 ላይ እግዚአብሄር ለነብዩ የጎመራ ወይም የበሰለ ፍሬ ማሳየቱ፤ ከእስራኤል ሕይወት ጋራ በተገናኘ የሚሰጠው የፍሬው መብሰል የሚያሳየው ነገር ምንድነው? በቁ1-3 ላይ ከምናነበው፤ ጌታ እግዚአብሄር በሕዝቡ ላይ በሚፈርድበት ቀን ሊሆኑ ያላቸው ነገሮች ተጠቅሰው እናገኛለን፤ በዚያን በፍርድ ቀን በምድሪቱ ውስጥ እንደሚታዩ የተነገሩ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ የተጠቀሱትን ቢያንስ ሶስት ነገሮች ተናገር።
2. በ7፡4-6 ላይ ስናነብ አሞጽ መልዕክቱን በተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች ላይ አተኩሮ ሲናገር ነው የምንመለከተው፤ እነዚህ በዚህ ክፍል ውስጥ አሞጽ ትኩረት ሰጥቶ የሚያናግራቸው ሰዎች እነማን ናቸው? እነዚህ ችግረኞችንና የምድሪቱን ድሆች የሚበዘብዙት ሰዎች እንዴት አድርገው እንደሚበዘብዟቸው እቅድ ሲያወጡ ስንመለከት፤ የምድሪቱ ችግረኞችና ድሆች ከእነዚህ ሰዎች ክፋትና ተንኮል ራሳቸውን ለመከላከል ሲያደርጉ የምናየው ምን ነገር አለ? እነዚህን ቁጥሮች ስናነብ ለድሆቹና ለችግረኞቹ ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ሲሟገት የምናየው ማን እንደሆነና በተጨማሪም ደግሞ ይህንኑ ሃሳብ የሚያጠናክር የመጽሐፍ ቅዱስ የመደገፊያ ሃሳብ ተናገር።
3. በእግዚአብሄር ሕዝብ ላይ ሊመጣ ያለው ቁጣና መከራ ምን ያህል አስከፊ እንደሚሆን ቁ8-10 ውስጥ የምናነበው ሃሳብ በምን ዓይነት መንገድ ነው የሚገልጽልን? በተለይ ቁ10ርን ስንመለከት "ያን ጊዜ ለአንድያ ልጅ ሞት እንደሚለቀስበት ፍጻሜውንም እንደመራራ ቀን አደርገዋለሁ።" የሚለው አነጋገር፤ እግዚአብሄር በእነርሱ ወገን ሆኖ ይህንን ዓይነት ለቅሶ ያስለቀሰበት የትኛው ቀን ሊታሰባቸው ይችላል ትላለህ?
4. አሞ 9፡1-4 ላይ ነብዩ ከእግዚአብሄር ስለመሸሽ በሚናገረውና ዳዊት ደግሞ በመዝ 139፡7-12 ላይ ይህንኑ ሃሳብ በመመርኮዝ የሚናገረውን ነገር ስንመለከት፤ ሁለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንድነት በመመልከት ማጠቃለያ አድርገን ልንወስደው የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው? በቁ4 ላይ "ለመልካም ሳይሆን ለክፉ፣ ዓይኔን በእነርሱ ላይ አደርጋለሁ።" ሲናገር ከላይ በቁ1-3 ውስጥ ካነበብናቸው ሃሳቦች ጋራ የሚገናኘው በምን መንገድ እንደሆነ ነው ለአንተ የሚታይህ?
5. አብዛኛውን ጊዜ እኛ የምናውቀውና መጽሐፍ ቅዱሳችንም በተደጋጋሚ የሚነግረን እግዚአብሄር እስራኤልን ከግብጽ ምድር እንዳወጣ ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ በተለይም በቁ7 ላይ እግዚአብሄር እንደ እስራኤል የታደጋቸው የሚነግረን የሁለቱ ነገሥታት ስም ማንና ማን እንደሆነ ተናገር። በአሞ 9፡5-8 ውስጥ የእግዚአብሄር ዓይኖች በሃጥያተኛ መንግሥት ላይ እንደሆነ ይናገራል፤ ቁ4 ላይ የእግዚአብሄር ዓይኖች በሕዝቡ በእስራኤል ላይ አደርጋለሁ ብሎ ከተናገረ፤ ሁለቱን ጥቅሶች በመመልከት እግዚአብሄር በፍርዱ ጻድቅና የማያዳላ እንደሆነ የምንማረው እንዴት ነው?
6. በቁ9 ላይ እግዚአብሄር አምላክ የእስራኤልን ቤት እህል በወንፊት እንደሚነፋ በህዝብ ሁሉ መካከል እንዲሁ እንደሚያደርጋቸው ሲናገር እንመለከተዋለን። ይህንን የእግዚአብሄር አነጋገር በቁ8 ላይ ከሚናገረው ሃሳብ ጋራ ስናገናዝበው ልንደርስበት የምንችለው መደምደሚያ ሃሳብ ምን ሊኖን ይችላል ትላለህ? ቁ8 እና ቁ9 ከተናገሩት ሃሳቦች ጋራ በተያያዘ ቁ10 ደግሞ እግዚአብሄር ከሕዝቡ መሃል ያሉና ሊቀጣቸው የወሰነ ዓይነት ሰዎችን ያሳየናል፤ እነዚህ ሰዎች ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው?
7. ቁ11-13 ላይ በተለይም ቁ13ትን ስንመለከት እግዚአብሄር ለሕዝቡ ሊያደርግ ያለውን ነገርና ከፊታቸው ሊመጣ ያለውን መልካም ዘመን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው አስገራሚ አነጋገሮች ምን እንደሆኑ ተናገር። በቁ14 እና በቁ15 ላይ እግዚአብሄር ስለ እስራኤል የወደፊት ነገርን ከተናገራቸው የትንቢት ቃሎች መካከል ተፈጻሚነትን እንዳገኙ የምናውቃቸውን ጥቂት ሃሳቦች በመዘርዘር ለመናገር ሞክር።
8. ወደ ኋላ ተመልሰን ስናይ፤ በምዕራፍ 7 ውስጥ ካህኑ ሳይቀር የእግዚአብሄርን ቃል የመስማት ፍላጎት እንዳልነበረው እንዲያውም ነብዩን ያሳድድ እንደነበረ፤ በ8፡11-12 ላይ ደግሞ የእግዚአብሄር ቃል ለመስማትና ለማግኘት ሰዎች እንደሚሞክሩ ነገር ግን እንደማያገኙ እናነባለን። የእግዚአብሄርን ድምጽ በመናቃቸው ሊመጣባቸው ያለው የእግዚአብሄር ቃል ረሃብ፤ በዚህ ዘመን ላለነውስ አማኞችስ ምን ትምህርት ሊሆነን ይችላል ትላለህ? ዛሬ የእግዚአብሄር ቃል በሰፊው ያለ አንዳች ገደብ ማንበብና ማጥናት በምንችልበት ጊዜ ካልተጠቀምንበት፤ ወደፊት ዛሬ ያለን ዓይነት ነጻነት ሁልጊዜ ይኖረናል ብሎ ማሰብ ሞኝነት ይሆናል።